UW Medicine
UNIVERSITY OF WASHINGTON MEDICAL CENTER

# በእርግዝና ወቅት የሚታዩ የችግር ጠቋሚ ምልክቶች

*መቼ መደወል እንዳለብዎት*

**ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የችግር ጠቋሚ ምልክቶችን ከተመለከቱ ወዲያዉኑ ወደ ጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጭዎ ይደውሉ።** ችግሮችን አስቀድሞ አውቆ ለችግሮቹ መፍትሔ ማግኘት፣ በእርስዎና በህጻን ልጅዎ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ችግር ዘውትር ይቀንሳል።

## ሰውነትዎ የሚነግርዎ ጠቋሚ ምልክቶች

- ከብልትዎ ደም ሲፈስ ወይም ሲንጠባጠብ
- ከብልትዎ ውሃ መፍሰስ ወይም መንጠባጠብ ሲጀምር
- ከ 37 ሳምንት በታች ለሚሆን ግዜ አርግዘው ከሆነ፣ ብልትዎ አካባቢ ህመም ሲሰማዎ ወይም በሰዓት 6 ወይም ከዚያ በላይ ለሚሆን ግዜ ቁጥርጥር የማለት ስሜት ከተሰማዎ
- ከግዜው በፊት የሚከሰት የምጥ ምልክቶች፤
  - እንደ የወር አበባ ዓይነት ህመም
  - ታችኛው ጀርባ አካባቢ የሚሰማ መጠነኛ ህመም
  - ዳሌ አካባቢ ጭና ወይ ክብደት ሲሰማዎ
  - የአንጀት ህመም፣ ከተቅማጥ ጋር ወይም ያለ ተቅማጥ
  - ከብልት ውስጥ የሚፈስ ፈሳሽ መጨመር ወይም ዓይነት ሲቀይር
  - “የሆነ ችግር አለ” የሚል ስሜት ሲሰማዎ
- ሆድዎ ላይ የሚወጋ፣ የማያቋርጥ ህመም
- ከ 100.4°F (38°C) በላይ ትኩሳት
- የማይሄድ የማቅለሽለሽ ስሜት ወይም ማስታወክ
- ምናልብት ሊከሰት የሚችል ከግዜ በፊት የሚጀምር ምጥ (የደም ብዛት)፣ አብዛኛውን ግዜ ከ 20 ሳምንት እርግዝና በኋላ፤
  - ድንገት የሚከሰት የፊት፣ እጆች ወይም እግር ማበጥ
  - ካረፉ በኋላ፣ acetaminophen (Tylenol)፣ እና ውሃ ከጠጡ በኋላ እንኳን የማይድን የማያቋርጥ የራስ ምታት
  - የዓይን መደብዘዝ፣ የብርሃን ብልጭታ ወይም ጠቃ ጠቆ በዓይንዎ ፊት ላይ ማየት



*የሆድ ህመም ወይም ሌሎች የችግር ጠቋሚ ምልክቶች ከተመለከቱ፣ ወደ ጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎ ወዲያዉኑ ይደውሉ።*

- በሚሸኑበት ወቅት ህመም ወይም የመቃጠል ስሜት (ወይም ሁለቱም) ከተሰማዎ
- ኩፍኝ (ሚዝልስ)፣ ጀርማን ሚዝልስ፣ ቺክን ፖክስ፣ ወይም እርስዎ የሚፈሩት ሌላ በሽታ ካለው ሰው ጋራ ተገናኝተው ከነበረና፣ ለነዚያ በሽታዎች መከላከያ ክትባት ተከትበው ካልነበረ

## ልጅዎ የሚያሳይዎ የችግር ጠቋሚ ምልክቶች

ልጅዎ ምን ያህል እንደሚንቀሳቀስ ይታዘቡና፣ ልጅዎ የሚያደርጋቸውን የተለመዱ እንቅስቃሴዎችንንና ተግባሮችን መቀነሱን ከታዘቡ፣ ወደ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎ ይደውሉ። ከ 28 የእርግዝና ሳምታት ወዲህ ጀምሮ ህጻን ልጅዎ በ 2 - ሰዓት ግዜ ውስጥ፣ ቢያንስ ለ 10 የተለያዩ ግዜዎች መንቀሳቀስ ይኖርበታል።

*ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እርግዝና፣ የህጻን ልጅ ወሊድነትና አዲስ የተወለደ ሕጻን (Pregnancy, Childbirth and the Newborn)* ይመልከቱ።

### ጥያቄዎች?

ጥያቄዎቻችሁ በጣም አስፈላጊ ናቸው። በእርግዝና ወቅት ስለሚኖሩ የችግር ጠቋሚ ምልክቶች ጥያቄዎች ካልዎት፣ በስራ ሰዓት ላይ ወደ ጤና እንክብካቤ አገልግሎት ስጭዎ ይደውሉ።

የአገልግሎት ሰጪዎ ቢሮ ከተዘጋ፣ ወደ UWMC Labor & Delivery በዚህ ስልክ ቁጥር ይደውሉ፤ 206-598-4616

© University of Washington Medical Center
Warning Signs During Pregnancy – Amharic
Published PFES: 07/2003, 12/2007, 12/2012
Clinician Review: 12/2012
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu

UW Medicine
UNIVERSITY OF WASHINGTON MEDICAL CENTER

# Warning Signs During Pregnancy

*When to call*

**Call your health care provider right away if you have any of these warning signs.** Noticing and dealing with problems early can often lower risks for you and your baby.

## Your Body's Warning Signs

- Bleeding or spotting from your vagina
- A gush or leak of water from your vagina
- Uterine cramping or tightening 6 or more times an hour if you are less than 37 weeks pregnant
- Symptoms of preterm labor:
  - Menstrual-like cramping
  - Dull, low backache
  - Pelvic pressure or heaviness
  - Intestinal cramping, with or without diarrhea
  - Increase or change in the character of vaginal discharge
  - General feeling that "something is not right"
- Sharp, constant pain in your belly
- Fever over 100.4°F (38°C)
- Nausea or vomiting that will not go away
- Possible signs of pre-eclampsia (high blood pressure), usually after 20 weeks of pregnancy:
  - Sudden swelling of your face, hands, or feet
  - Constant bad headache that will not go away after resting, taking acetaminophen (Tylenol), and drinking water
  - Blurred vision, flashes of light, or spots in front of your eyes



*Call your health care provider right away if you have cramping or any other warning signs.*

- Pain or burning (or both) when you urinate
- Contact with someone who has measles, German measles, chicken pox, or other illnesses you are concerned about, if you have never been vaccinated or had these illnesses

## Your Baby's Warning Signs

Also be aware of how your baby is moving, and call your health care provider if you notice a decrease in your baby's normal movements and activity. Starting at 28 weeks of pregnancy, your baby should move at least 10 separate times in a 2-hour period every day.

See *Pregnancy, Childbirth and the Newborn* for more information.

### Questions?

Your questions are important. If you have questions about warning signs during pregnancy, call your health care provider during office hours.

When your provider's office is closed, call UWMC Labor & Delivery: 206-598-4616

© University of Washington Medical Center
Published PFES: 07/2003, 12/2007, 12/2012
Clinician Review: 12/2012
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu